# ነፃ ስልጠና በኖርዌጅኛ ቋንቋ እና በህብረተሰብ ትምህርት

**የኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስልጠና በነፃ ስለማግኘት መብት**

በኖርዌይ አገር የመኖሪያ ፈቃድ ሲያገኙ በጠቅላላ ለ 300 ሰዓታት ያህል ስልጠና ፥ ማለትም፤
♦ ለኖርዌጅኛ ቋንቋ 250 ሰዓታት እና
♦ ለህብረተሰብ ትምህርት 50 ሰዓታት ነፃ የስልጠና መብት ይኖረዎታል ።

ስልጠናው ለሶስት ዓመታት ያህል በነፃ የሚሰጥ ሆኖ ተግባራዊ የሚሆነው ፥
♦ የመኖሪያ ፈቃድ ካገኙበት ቀን ጀምሮ ወይም
♦ ወደ ኖርዌይ ህጋዊ ፍቃድ ይዘው ከገቡበት ቀን አንስቶ ሊሆን ይችላል።

እላይ በተጠቀሱት ሶስት ዓመታት ስልጠናዉን ካልጀመሩ ወይም ካላጠናቀቁ ስልጠናውን ከፍለው እንዲወስዱት ይደረጋል ።

**የኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስልጠና ስለመውሰድ ግዴታ**

የኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስልጠናውን በ 300 ሰዓታት የማጠናቀቅ ግዴታ የሚያስፈልገው፥
♦ ቋዋሚ የነዋሪነት ፈቃድ እና /ወይም
♦ የዜግነት መብት ለማግኘት ማመልከቻ ለማቅረብ ይሆናል ።

ይህ የስልጠና ግዴታ በምዝገባ ወቅት ዕድሜዎ 55 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ግን ተፈፃሚነት አይኖረውም።

ከስልጠናው ግዴታ ነፃ ለመሆን ማመልከት የሚችሉት፥
♦ የኖርዌጅኛ ወይም የሳሚኛ ቋንቋዋ በቂ ችሎታ ያሉዎት መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ ወይም
♦ በተለይ ደግሞ የጤና እክል ወይም ሌላ አሳማኝ ምክንያት ካለዎት ይሆናል ።

**ተጨባጭ መረጃ**

ስልጠናውን ለመውሰድ ወይም ላለመውሰድ መረጃ ከፈለጉ በተመዘገቡበት የህዝብ ምዝገባ ፅህፈት ቤት አቅራቢያ በሚገኘው የማዘጋጃ ቤቱ /ኮሚን / የጎልማሶች ማሰልጠኛ ማእከል በአካል ቀርበው ማመለከት ይችላሉ ። የምዝገባ ቀን ማጠናቀቂያ ለማወቅ ወይም መብትዎን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት ወይም መረጃ ከፈለጉ ከማሰልጠኛ ማእከሉ ጋር መገናኘት ይችላሉ።

ተጨማሪ መረጃ ከሚከተሉት ድረ ገፆት ማግኘት ይችላሉ።

www.imdi.no እና www.udi.no.